# የጤና ባለሙያዎች የሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ

# <u>መመሪያ</u>

Directive on Health Professionals Ethics Committe

## የቤኒሻንጉል- ጉሙዝ ክልል መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ

ታህሳስ/2008 ዓ.ም

<u>አሶሳ</u>

የጤና ባለሙያዎች የሥነ-ምግባር ኮሚቴን ተግባር፤ሃላፊነት፤ይዘትና እና የአሰራር ሂደቱንበግልጽ በሚያሳይ መልኩ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖበመገኘቱ፤

የጤና ባለሙያዎች ሙያዊ አሰራርን በተመለከተ ግልጽና ህጋዊ ስርዓት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የታካሚዎችን መብት ለማስጠበቅና የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሙያ ሥነ-ምግባር ጉዳዮች ተገቢው ትኩረት እንዲሰጣቸው ለማድረግ፤

የሕክምና አሰጣጥ ጥራቱን የጠበቀና የታካሚዎችን ፍላጎት ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በመሆኑም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/2007 ዓ/ም አንቀጽ 86 መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

Directive on Health Professionals Ethics Committe

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1

### አጭርርዕስ

ይህ መመሪያ "የጤና ባለሙያዎች የሥነ-ምግባር መከታተያ መመሪያ ቁጥር02/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

1. "የጤና ባለሙያ" ማለት የሰውንጤናለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስጠት በባለስልጣኑእንደ ጤናባለሙያ የተመዘገበ ሰው ነው፤

2. **“የጤና ተቋም”** ማለት መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ሆኖ ጤናን የማበልፀግ፣ በሽታን የመከላከል ወይም የፈውስ ሕክምና የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

3. **“ኮሚቴ”** ማለት የጤና ባለሙያዎችን ስነ-ምግባር ለመቆጣር የተቋቋመ አካልነው።

4. **“ቅሬታ”** ማለት ከህክምና አገልግሎት፣ ከባለሙያ ብቃት እና ስነ-ምግባር ጉድለት ጋር ተያይዞ ለኮሚቴው በጽሁፍ የሚቀርብ ማመልከቻ ነው።

5. **“የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት”** ማለት ለአንድ ሰው የሕክምና ስራ ማከናወን ይችል ዘንድ የተሰጠው ማረጋገጫ ማለት ነው።

6. **“የሙያ ስራ ፈቃድ”** ማለትየጤናአጠባበቅአገልግሎትወይምሌሎችተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማበርከት እንዲችል ለጤና ባለሙያ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው።

7. **“ቢሮው”** ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ ማለትነው።

8. **“የስራ ሂደቱ”** ማለት የጤናና ጤና ነክ አገልግሎት እና ግብዓት ጥራት ቁጥጥር ዋና የስራ ሂደት ነው።

9. **“ሰው”** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

10. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## <u>**አንቀጽ 3**</u>

## <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ መመሪያ ባለስልጣኑ በሚቆጣጠራቸው የጤና ባለሙያዎች ላይ በሚቀርብ ቅሬታላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>**አንቀጽ 4**</u>

## <u>**መሰረታዊ መርሆዎች**</u>

1. የሥነ-ምግባር ኮሚቴው በማንኛውም ጊዜ የታካሚውን፣ የጤና አገልግሎትተጠቃሚዎችና የሕዝቡንፍላጎት መጠበቅና ማርካት አለበት።
2. በሥነ-ምግባር ኮሚቴው የሚተላለፍ የአሰራር ሂደቶችና ውሳኔዎች በሀገሪቱ ካሉ ሕጎችና አግባብ ካላቸውየሙያ መርሆዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው።
3. ማንኛውም የሥነ-ምግባር ኮሚቴ አባል ምን ጊዜም ሙያዊ ስነ-ምግባሩን መጠበቅ አለበት።

Directive on Health Professionals Ethics Committe

4. በሥነ-ምግባር ኮሚቴ በተላለፈ ውሳኔ ላይያልተስማማ ሰው ይግባኝ ሊል ይቻላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የስነ-ምግባር ኮሚቴ ተግባር፣ አደረጃጀት እና አወቃቀር

### አንቀጽ 5

### የኮሚቴው ተግባር

ኮሚቴው የሚከተሉት ስልጣን እና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. ከደረጃ በታች በሆነ የጤና አገልግሎት፣ብቃት በጎደለው እና የሙያውን ስነ-ምግባር ባልጠበቀ የአሰራር ሂደት የደረሱ ጉዳቶችን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ማየት፣ መፈተሽ እና የውሳኔ ሀሳብ ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተርማቅረብ፤
2. አቤቱታ ባይቀርብም የባለሞያዎችንየስነ-ምግባር ጥሰት የሚመለከት መረጃ ካለ የማጣራት ስራ መስራት፤
3. ክስ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ባለሞያእንደአግባቡ ቢያንስ በ30 ቀን ውስጥ ቀርቦ ስለቀረበበት ቅሬታ እንዲያስረዳ ጥሪ ማድረግ፤
4. አቤቱታውን ወይም ቅሬታውን በሚመለከት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከባለስልጣኑ ጋር በመመካከር ገለልተኛየሆነአጣሪ ባለሞያ መሰየም፤
5. ተግባሩን በአግባቡ እንዲወጣ ንዑስ ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ማቋቋም፤
6. አቤቱታ በቀረበበት ባለሙያ ላይ ጉዳዩ ተጣርቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የሞያ ስራ ፍቃዱንማገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝይህንኑ ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ፤
7. የስነ-ምግባር ጥሰት ያደረጉ ባለሞያዎችን የሞያ ፈቃድ ማገድ እና መሰረዝን ጨምሮ በዚህ መመሪያ መሰረት የተቀመጡ አግባብ ያላቸውን እርምጃዎች እንዲወሰዱማድረግ፤
8. በተደጋጋሚ የሚቀርቡት የባለሞያዎች ስነ-ምግባር ጥሰትን ለመከላከል አስፈላጊውን የፖሊሲ አቅጣጫ እና የቁጥጥር ስርአትን በሚመለከት ለባለስልጣኑ ሀሳብ ማቅረብ፤ እና
9. ሌሎች ከተግባር እና ሀላፊነቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

### አንቀጽ 6

### የኮሚቴው አደረጃጀት

ኮሚቴው፡-

1. ዋና ሰብሳቢ፤
2. ምክትል ሰብሳቢ፤
3. ጸሃፊ፤ እና

Directive on Health Professionals Ethics Committe

4. አስፈላጊ የኮሚቴ አባላት ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ 7

## ዋና ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢን ስለመመደብ

1. የጤና ጥበቃ ቢሮው ኃላፊ ከኮሚቴው አባላት ውስጥ አንድ ሰብሳቢ ይመድባል፡፡
2. ኮሚቴው በሚያካሂደው የመጀመሪያ ስብሰባው ላይ የኮሚቴውን ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣል፡፡
3. ዋና ሰብሳቢ በሌለበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው የዋናውንሰብሳቢ ስልጣን እና ኃላፊነትን በሙሉ ይተገብራል፡፡
4. ዋና ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢበማይኖሩበት ጊዜ የሰብሳቢነትስልጣን እና ኃላፊነትን እንዲወጣ ኮሚቴው ከአባላት ውስጥ አንድ ሰብሳቢ ሊመርጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 8

## የዋና ሰብሳቢ ስልጣንና ኃላፊነት

የኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ፡-

1. የኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳ ያቀርባል፣ ይወስናል፤
2. የኮሚቴውን ስብሰባ በበላይነት ይመራል፤
3. የኮሚቴው አባላት በዚሁ መመሪያ እና ሌሎች አግባብ ባላቸውየሀገሪቱ ህጎች መሰረት ተግባራቸውን መወጣታቸውን ይከታተላል፣
4. ማንኛውም የኮሚቴ አባል የስነ-ምግባር ግድፈት አለበት ብሎ ካመነ ለጤና ጥበቃ ቢሮው ኃላፊ ያሳውቃል፤
5. ማንኛውንም ቅሬታ እና የኮሚቴውን ስራ በተመለከተ ከጤና ጥበቃ ቢሮው ኃላፊ ጋር መረጃ ይለዋወጣል፤
6. ለቢሮው ኃላፊኮሚቴው ያስተላለፈውን የመጨረሻ የውሳኔ ሀሳብ በጽሁፍ ያሳውቃል፤ እና
7. ሌሎች ቢሮው ወይም በኮሚቴው የሚሰጡትን ተጨማሪ ሀላፊነቶችን ይፈጽማል፡፡

## አንቀጽ 9

## የጸኃፊአመዳደብ እናኃላፊነት

1. ቢሮውእንደ አግባቡ ሙሉ ጊዜውን በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (2) መሰረት የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚፈጽምየህግባለሙያይመድባል፡፡
2. ጸሃፊው፡-

   (ሀ) የቅሬታ እና ተያያዥ ሰነዶችን ይቀበላል፣ ይይዛል፣ ለዋና ሰብሳቢ ያቀርባል፤

   (ለ) የኮሚቴውን የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፤

Directive on Health Professionals Ethics Committe

(ሐ)በቀረቡ ቅሬታ እና ማስረጃዎችላይ የተጓደሉካሉ እንደአስፈላጊነቱእንዲሟሉወይም እንዲስተካከሉ ያደርጋል፤

(መ) የስብሰባ ጊዜን ለኮሚቴው አባላት እና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤

(ሠ)ለኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ የስብሰባ አጀንዳን፣ ቀንን እና ተያያዥጉዳዮችን በተመለከተ ሀሳብ ያቀርባል፤

(ረ) በቃለ ጉባኤ የተያዙትን የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በጽሁፍ ያዘጋጃል፣ ለሰብሳቢውእናለቢሮ ኃላፊው ያቀርባል፤

(ሰ) የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ የሚያስለውጥ ወይም በውሳኔ ሀሳቡ ላይ ተጽእኖ ሊኖራቸው የሚችል እውነታዎችወይም መረጃዎችካሉለኮሚቴው ወይም ለዋና ሰብሳቢው ያሳውቃል፤

(ሸ)ሌሎች በኮሚቴው የሚሰጡትን ተጨማሪ ሀላፊነቶችን ይፈጽማል፡፡

## አንቀጽ 10

## የኮሚቴ አባላት ምርጫ እና የቆይታ ጊዜ

1. አንድ ሰው የኮሚቴ አባል ሆኖ መስራት የሚችለው ከተመረጠበት ቀን አንስቶ ከ3ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፡፡በዚህ መሰረት ቀድሞ የኮሚቴ አባል ሆኖ የሰራ ማንኛውም ሰው በድጋሚ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሊመረጥ ይችላል፤
2. የኮሚቴ አባል ሆኖ ሊመረጥ የሚችል ሰው፡-
   (ሀ) ባለሙያ ከሆነ ቢያንስ የአምስት አመት ልምድ ያለው፤
   (ለ) የጤና ባለሙያ ከሆነ ህጋዊ የሙያ ስራ ፈቃድ ያለው፤
   (ሐ)በስነ-ምግባሩ የተመሰገነ እናበስራው ላይ ተጽእኖ ሊያደርስ የሚችል የእምሮ ህመምየሌለበት፣
   (መ)ከማንኛውም ዕጽ እና በስራው ላይ ተጽእኖ ሊያደርስ ከሚችል ሱስ ነጻ የሆነ፤
   (ሠ) በህግ መብቱ ያልተገደበ፤
   (ረ)ከሙያው ጋር በሚገናኝ ወይም ለህሊና ተጻራሪ በሆነ ወንጀልተከሶ ጥፋተኛያልተባለ፤
   (ሰ) ህብረተሰቡን በቅንነት ለማገልገል ፍላጎት ያለው፡መሆን አለበት፡፡
3. በኮሚቴ አባል የሚፈጸምን ማንኛውንም አይነት የስነ-ምግባር ግድፈት እንዳለ የተረዳ የኮሚቴ አባል ጉዳዩን በሚመለከት ለኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤
4. የኮሚቴው አባላት የሚመረጡት ከሚከተሉት ዘርፎች ይሆናል፡-
   (ሀ)ከቢሮው ጤናና ጤ/ነ/አገ/ግ/ጥ/ቁ/ ዋና የስራ ሂደት (2)፤

(ለ)ከቢሮወ የፈውስ ህክምናና ተሀድሶ ዋ/ስ/ሂ፣ የሰው ኃ/ደ/ስ/ሂ፣ የህግ እና ስነ-

Directive on Health Professionals Ethics Committe

ምግባር ክፍሎች የተወጣጡ አንድ አንድ በድምሩ አራት ባለሙያዎች፤

(ሐ) ከተለያዩ የጤና (የህክምና) ማህበራት (2)

(መ) የህክምና ትምህርት ከሚያስተምሩ ተቋማት/ሆስፒታሎች (2) ፤

(ሠ)ከተገልጋዩ ማህበረሰቡ የሚውጣጡ ሁለት ተወካዮች፤ እና

(ረ) እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች መ/ቤቶች (2) ፡፡

## አንቀጽ 11

## የኮሚቴው ስብሰባ

1. ኮሚቴው ስራውን ለመስራት በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ(1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ ጠሪነት ኮሚቴው አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፤
3. ኮሚቴው የሚያካሂደው ማንኛውም ስብሰባበቃለ ጉባኤ የሚያዝ ይሆናል፤
4. ከኮሚቴው አባላት 50 % +1 ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤
5. ኮሚቴው ውሳኔ የሚያስተላልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ድምጹ እኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ወገንሀሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፤
6. በኮሚቴው የተላለፈውን ማንኛውም ውሳኔ እና ድርጊት በብዙሀኑ የተወሰነ ስለሆነ በስብሰባው ላይ ያልተገኘ አባልም ውሳኔውን ይቀበለዋል፤
7. የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ የሚጸና ሲሆን ውሳኔው በቢሮው ኃላፊ ከመጽደቁ በፊት ውሳኔውን ሊያስቀይር የሚችል በቂ ማስረጃ ሲገኝ ኮሚቴው ጉዳዩን በድጋሚ ሊያየው ይችላል፤
8. የኮሚቴው አባል የሆነ ከራሱ እና ከዝምድና ጥቅም ጋር በተያያዘ አሊያም ተወክሎ የመጣበትን ተቋምንም ሆነ አምሳያ ተቋማትን በማስመልከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች ሲታዩ ጉዳዩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከኮሚቴው አባልነት በጊዜያዊነት ይነሳል፤
9. ቅሬታ አቅራቢው አንድ የኮሚቴው አባል ጉዳዩን እንዳያይበት በጠየቀ ጊዜ እና በቂ ማስረጃ ቀርቦ ኮሚቴው በአብላጫ ድምጽ ሲወሰን ጉዳዩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከኮሚቴው አባልነት በጊዜያዊነት ይነሳል፡፡

## አንቀጽ 12

## ኮሚቴውስለማይቀጥልበት ሁኔታዎች

1. ቢሮው ኮሚቴው ተግባር እና ሀላፊነቱንበአግባቡ አልተወጣም ብሎ ካመነገለልተኛ አካል በመሰየም አስፈላጊውን የማጣራት ስራ እንዲከናወን ማድረግ ይችላል፤
2. ቢሮው ኮሚቴው በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጠውን ተግባር እና ሀላፊነቶችበአግባቡ ካልተወጣ ኮሚቴው እንዲፈርስ ሊያዝ ይችላል፡፡

Directive on Health Professionals Ethics Committe

## አንቀጽ 13

## ከአባልነት ስለማገድ ወይም ስለማሰናበት

ማንኛውም ሰው ከኮሚቴ አባልነት ሊታገድ ወይም ሊነሳ የሚችለው፡-

1. የሙያ ስነ-ምግባር ግድፈት ሲፈፅም፤
2. በዚህ መመሪያላይ የተቀመጡትን ሀላፊነቶች ለመወጣት አካላዊ ወይም አእምሮአዊ የጤና ችግር ከደረሰበት፤
3. እንደ ስርቆት፣ ማጭበርበር፣በሀሰት ሰነዶችን መጠቀም፣ ሙስና ወይም ሌሎች ታማኝነት የጎደላቸው ድርጊቶች እና ለህሊና ተጻራሪ በሆነ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፤
4. በበጀት አመቱ ሶስት ተከታታይ ወይም ኮሚቴው ካካሄዳቸው ስብሰባዎች በአጠቃላይ ስድስት ስብሰባዎች ያለፈቃድ ከቀረ፤
5. መልቀቂያ ለሚኒስቴሩ በራሱ ፍላጎት አቅርቦ ተፈቅዶለት ከሆነ፤
6. የኮሚቴውን አሰራር እና መልካም ስም ሊያጎድፍ የሚችል ወይም የሚፃረር የግል ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ከሆነ፤
7. በዚህ መመሪያ መሰረት ኮሚቴው ተግባሩን እንዳይወጣ እንቅፋት ሆኗል ብሎ ኮሚቴው ካመነ፤ ወይም
8. ተቀባይነት ባላቸው ሌሎች ምክንያቶች፡፡

## አንቀጽ 14

## ንዑስ ኮሚቴዎች

1. ንኡስ ኮሚቴው ዋና ኮሚቴው ባዘዘው መሰረት ስራውን ያከናውናል፡፡
2. በዚህ መመሪያ መሰረት በኮሚቴውየተቋቋመንኡስ ኮሚቴ ከአባላቱ የተሰየመ የራሱ ሰብሳቢ እና ጸሃፊ ይኖረዋል፡፡
3. ንዑስ ኮሚቴው፡-

   (ሀ) በተዘጋጀው ቅፅ መሰረት ለከሳሽ ወይም ቅሬታ ለቀረበለት አካል ጥሪ ያደርጋል፤

   (ለ) ከባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ ጋር በመሆን አስፈላጊውን ማስረጃ ይሰበስባል፣ በጽሁፍ የተደገፈ ማረጋገጫ ይወስዳል፣

   (ሐ)ከቢሮው ተቆጣጣሪ ጋር በመሆን ለማስረጃ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ወይም ሌሎችማስረጃዎችን ይፈትሻል፣ ይይዛል፤እና

   ‹መ) ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን ሊፈጽም ይችላል፡፡

**ክፍልሦስት**

## የቅሬታ አቀራረብ፣ ምርመራ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

## አንቀጽ 15

Directive on Health Professionals Ethics Committe

## የቅሬታ አቀራረብ

1. ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው ጉዳት በደረሰበት ግለሰብ፣ በአሳዳጊ፣ በተወካዩ ወይም ሌላ ጉዳዩ ይመለከተኛል በሚል አካል ሊሆን ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርብ ቅሬታ ጉዳዩ በታወቀ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እና በማንኛውም ሌላ ምክንያት በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ለኮሚቴው ፀሀፊ መቅረብ ይኖርበታል፤
3. ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው በፅሁፍ ሆኖ የቅሬታውን ዝርዝር ሁኔታ፣ በባለሙያው ላይ የታየው ግድፈት፣ የባለሙያው ሙሉ ስምና አድራሻ እና የቅሬታ አቅራቢውን ወይም የእሱን ህጋዊ ተወካይ ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡ ቅሬታ አቅራቢው በኮሚቴው ፀሀፊ የሚቀርብለትን ቅጽ በአግባቡ መሙላት አለበት፤
4. ቅሬታ አቅራቢው ምስክሮች ወይም ቅሬታውን የሚያጠንክሩለት ማስረጃዎች ካሉት፤ የምስክሮቹን ስም ዝርዝር እና የማስረጃ ሰነዱን ኮፒ ከቅሬታ ማመልከቻ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፤
5. የኮሚቴው ፀሀፊ ቅሬታ ለቀረበበት ሰው የቀረበበትን የቅሬታ ዝርዝር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 16
## ቅድመ ማጣሪያ ሂደት

1. ኮሚቴው በዚህ መመሪያ መሰረት በቀረበ ቅሬታ ላይ የማጣሪያ ስራ ለማካሄድ የቀረበው ማስረጃ በቂ ሆኖ ካላገኘው ከተከሳሽ ጨምሮ ከሌላ ማንኛውም አካል ተጨማሪ ማስረጃ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (1) መሰረት በሚሰበሰብ ማስረጃ መሰረት ግድፈት ተፈጽሟል የሚያስብል ምክንያት ከተገኘ ኮሚቴው ምርመራ ያካሂዳል፡፡
3. ኮሚቴው የመጨረሻ የውሳኔ ሀሳብ ከመስጠቱ በፊት የቀረበለትን አቤቱታ ወይም የጉዳዩን ባህሪ መሰረት በማድረግ ባለሙያው የጤና አገልግሎት እንዳይሰጥ የሙያ ፍቃዱን በጊዜያዊነት እንዲታገድ ሊያደርግ ወይም የተወሰኑ ሙያዊ ተግባራትን ብቻ እንዲያካሂድ ሊያዝ ወይም ይህንኑ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3) መሰረት የተላለፈው የእገዳ ወይም የክልከላ ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ከ60 ቀን መብለጥ የለበትም፡፡
5. አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ ላይ ኮሚቴው ምንም ዓይነት አሳማኝ ማስረጃ ካላገኘበት እገዳውን ወይም ክልከላውን ወዲያውኑ ማንሳት አለበት፡፡

Directive on Health Professionals Ethics Committe

## አንቀጽ 17

## ክስን ስለመከላከል እና እንዲነሳ ስለመጠየቅ

1. ቅሬታ እንደቀረበበት ያወቀና ቀርቦ መከላከል እንዳለበት በኮሚቴው ፀሀፊ አማካኝነት የተነገረው ቅሬታ የቀረበበት ባለሙያ ክሱ በደረሰው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ እንደ አግባቡ ምስክሮችን እና ማስረጃዎች ካሉት ይህንኑ በማካተት የክስ መከላከያ መልስ ማቅረብ አለበት፤
2. የቀረበው የክስ መከላከያ መልስ ቢያንስ የቅሬታ አቅራቢውንና ቅሬታ የቀረበበትን ግለሰብ ስምና ሙሉ አድራሻ፣ ለእያንዳንዱ የክስ ዝርዝር የቀረበ የመከላከያ መልስ ሙሉ መግለጫ እንዲሁም እንደአግባቡ የምስክሮች ሙሉ ስምና አድራሻ እና  የማስረጃ ሰነድ ኮፒ መካተት አለበት፤
3. የኮሚቴው ፀሀፊ ለቅሬታ አቅራቢው በተከሳሽ የቀረበውን የክስ የመከላከያ መልስ ኮፒ እንዲወስድ ይነግራል፤
4. አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ በቀረበበት የክስ ፍሬ ነገር ላይ አንድ በአንድ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የመከላከያ መልስ ካላቀረበ መከላከያ መልስ ያልቀረበበት ፍሬ ነገርን በሚመለከት እንዳልተከላከለ እና ክሱን እንደተቀበለው ይቆጠራል፤
5. ክስ የቀረበበት ባለሙያ በቀረበው ክስ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ክሱ እንዲነሳለት መጠየቅ የሚችለው የቀረበው ክስ፡-

   (ሀ) በዚህ መመሪያ መሰረት ለኮሚቴው ከተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት ውጪ ከሆነ፤

   (ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 (2) መሰረት የጊዜ ገደቡ ያለፈ ከሆነ፤ ወይም

   (ሐ) ከዚህ በፊት በኮሚቴው ክሱ የተነሳለት ከሆነ ወይም የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ይሆናል፤

6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (5) መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከቀረበ ኮሚቴው የክሱን ፍሬ ነገር ከመመልከቱ በፊት በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፤
7. ኮሚቴው የክሱን ፍሬ ነገር መመልከት ከጀመረ በኋላ ምንም ዓይነት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማቅረብ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 18

Directive on Health Professionals Ethics Committe

**ቅሬታን ወይም የመከላከያ መልስን ስለማሻሻል**

1. ማንኛውንም ቅሬታ ወይም በቅሬታ ላይ የሚቀርብ የመከላከያ መልስ ለማሻሻል የሚቻለው ኮሚቴው አግባብ ነው ብሎ ካመነ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ብቻ ይሆናል፤
2. ኮሚቴው ውሣኔውን ለማስተላለፍ እንዲረዳው የቀረበው አቤቱታ ወይም የመከላከያ ሀሳብ መሻሻል እንዳለበት ካመነበት እንዲሻሻል ማዘዝ ይችላል፤
3. የቀረበው አቤቱታ የመከላከያ ወይም መልስ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከተሻሻለ ለሌኛው ተከራካሪ ወገን እንደ አግባቡ አቤቱታውን ወይም መልሱን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 19**

**ቅሬታን ስለማንሳት**

1. ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ለማንሳት የሚችለው በጽሁፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ሆኖ ጉዳዩ የህብረተሰቡን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑ ኮሚቴው ሲያምንበት እና ኮሚቴው የመጨረሻ የውሳኔ ሀሳብ ከመስጠቱ በፊት ብቻ ይሆናል፤
2. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (1) መሰረት የተነሳ ማንኛውም ቅሬታ ለኮሚቴው በድጋሚ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 20**

**ጥሪ ስለማስተላለፍ**

1. ኮሚቴው ጉዳዩን ለመስማት ከቀጠረበት አስር ቀናት በፊት የኮሚቴው ፀሀፊ የቅሬታውን ኮፒ ቅሬታ ለቀረበበት ባለሙያ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡የቅሬታውን ኮፒ ቀጥታ ለባለሙያው ሊሰጥ ወይም ባለሙያው መጥቶ እንዲወስድ ወይም ባለሙያው ካልተገኘ ለሚሰራበት ተቋም ሊሰጥ ይችላል፤
2. ቅሬታውን ያቀረበው አካል ወይም ቅሬታ ለቀረበበት ባለሙያ ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ እንዲገኝ አስፈላጊ ነው ብሎ ኮሚቴው ካመነ በፀሀፊው አማካኝነት የስብሰባው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በመጥቀስ እንዲቀርብ ጥሪ ይደረግለታል፡፡

**አንቀጽ 21**

**ጉዳዩን ስለማየት**

1. ኮሚቴው የመከላከል መልስ ከደረሰው በኋላ ጉዳዩን ለማየት ይሰበሰባል፤
2. ኮሚቴው መብራራት አለበት ብሎ ያመነበት ነገር ካለ የመጨረሻ ውሣኔ ከማስተላለፉ በፊት ጉዳዩን ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል፤
3. ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ፣ የመከላከያ መልስ እና ማስረጃዎችን ካየ በኋላ ውሣኔ ያስተላልፋል፤

Directive on Health Professionals Ethics Committe

4. በቅሬታ ማመልከቻው ላይ ከቀረበው የክስ ዝርዝር በተጨማሪ ኮሚቴው ሌላ ተያያዥ የስነ-ምግባር ግድፈት አለ ብሎ ካመነ በመጀመሪያ በቀረቡት የክስ ዝርዝሮች ላይ በመጨመር ጉዳዩ እንዲጣራ እና መከላከያ እንዲሰጥበት ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 22**

**ቅሬታ አቅራቢው ወይም ተከሳሹ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ሳይገኝ ሲቀር**

1. ተከሳሹ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ እንዲቀርብ በኮሚቴው ተጠርቶ ሳይቀርብ ከቀረ ኮሚቴው የቅሬታ አቅራቢውን ማስረጃዎች እና የምስክር ቃል ሰምቶ በተሰጠው መረጃ መሰረት የውሣኔ ሀሳብ ማስተላለፍ ይችላል፣
2. ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ መገኘት እንዳለበት የተነገረው ተከሳሽ ሳይገኝ የቀረበትን አሳማኝ ምክንያት በአስር ቀናት ውስጥ ለኮሚቴው ጸሀፊ ካቀረበ እና ኮሚቴው ካመነበት ጉዳዩ እንደገና ሊታይ ይችላል፣
3. ቅሬታ አቅራቢው ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ላይ መገኘት እንዳለበት ተነግሮት ሳይቀርብ ሲቀር ጉዳዩ የህብረተሰቡን ጥቅም የማይጎዳ ከሆነ ኮሚቴው የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ እንዲሆን ሊወስን ይችላል፣
4. ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ላይ መገኘት እንዳለበት የተነገረው ቅሬታ አቅራቢ ሳይገኝ ቀርቶ የቀረበበትን አሳማኝ ምክንያት በአስር ቀናት ውስጥ ለኮሚቴው ጸሀፊ ካቀረበ እና ኮሚቴው ካመነበት ጉዳዩ እንደገና ሊታይ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 23**

**ምስክሮች**

1. ኮሚቴው አሰፈላጊ ሆኖ ካገኘው በቀረበው ክስ ላይ ምስክሮች የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ጥሪ ያደርጋል፣
2. በተመሳሳይ ወይም ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአንድ ሰዓት እንዲቀርቡ የተጠየቁ ምስክሮች ምስክርነታቸውን ለየብቻቸው እንዲሰጡ ይደረጋል፣
3. ቅሬታ አቅራቢ ወይም ተከሳሽ ለምስክርነት ያቀረበውን ሰው እንዲቀርብ ለማድረግ የኮሚቴውን መጥሪያ የሚያደርሰው እነዚህኑ ምስክሮች የጠራቸው ወገን ነው፣
4. መጥሪያ አልቀበልም ያለ ወይም በመጥሪያ መሰረት ሳይቀርብ የቀረ ምስክር አግባብ ባለው የህግ አካል ተገዶ ምስክርነቱን ለኮሚቴው እንዲሰጥ ይደረጋል፣
5. የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ የተጠራ ምስክር በሚያዘው ቃለ ጉባኤ መሰረት እንዲፈርም ይደረጋል፣
6. ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ቅሬታ አቅራቢ ወይም ተከሳሽ በኮሚቴው ከተጠራ ለምስክር መስቀለኛ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 24**

Directive on Health Professionals Ethics Committe

**ሌሎች ማስረጃዎችን መመርመርና መቀበል**

1. ኮሚቴው ለጉዳዩ አስፈላጊ ይሆናሉ ብሎ ያመነበትን መረጃ ሁሉ ሊቀበል ይችላል፤
2. ኮሚቴው ውሣኔ ለማስተላለፍ ተጨማሪ ማረጋገጫ እና ምስክር ያስፈልጋል ብሎ ካመነበት ተጨማሪ ማረጋገጫ እና ምስክር እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፤
3. የጤና መረጃን፣ የህክምና መሣሪያ ወይም ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎችን የሚይዝ ማንኛውም የጤና ተቋም ኮሚቴውከባለስልጣኑ በሚወክለው አካል ጉዳዩን ለማጣራት አስፈላጊውን ምርመራ እንዲያደርግ መፍቀድ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 25**

**የውሣኔ ሀሳብ እና አፈፃፀም**

1. ኮሚቴው የመስማት ሂደቱን ካጠናቀቀ በኋላ ቢያንስ በሚቀጥለው የስብሰባ ጊዜ ውሣኔ ማሳለፍ አለበት፤
2. የመጨረሻ የውሳኔ ሀሳብ በተሰጠ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የኮሚቴው ጸሀፊ ውሳኔውን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለኮሚቴው ሰብሳቢ ወዲያውኑ እንዲፈረም ያቀርባል፤
3. የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በዋና ሰብሳቢ በተፈረመ በሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት  ውስጥ ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ይቀርባል፤
4. የውሳኔ ሀሳቡ በባለስልጣኑ ከጸደቀ እንደ አግባቡ ውሳኔው በተከሳሹ፣ በቀጣሪው፣ በፍቃድ ሰጪ አካል ወይም ሌሎች አስፈላጊ አካላት እንዲፈጸም ይደረጋል፤
5. ውሣኔው በዚህ መመሪያ መሰረት ይግባኝ ካልተባለበት በስተቀርበተከሳሽ ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ ወይም ተፈፃሚ ካልሆነ ቢሮው እንደ አግባቡ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ወይም ጉዳዩን አግባብ ላለውየህግ አስፈፃሚ አካል ማስተላለፍ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 26**

**አስተዳደራዊ እርምጃዎች**

1. የስነ-ምግባሩን ግድፈት ክብደት መሰረት በማድረግ ኮሚቴው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንድ ወይም ከዛ በላይ እርምጃ እንዲወሰድ ሀሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡-

(ሀ) የቃል ማስጠንቀቂያ፤

(ለ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፤

(ሐ)ስልጠናዎችን ወይም ተጨማሪ ትምህርት እንዲወስድ ማድረግ፤

(መ)በበሳል ባለሙያ ክትትል ስር ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ እንዲሰራማድረግ፤

(ሠ)ጥፋተኛ ከተባለበት ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሙያ ስራዎችን እንዳይሰራ ማገድ፤

Directive on Health Professionals Ethics Committe

(ረ)የሙያ ስራ ፍቃዱን ለተወሰን ጊዜ ማገድ፤

(ሰ)የሙያ ስራ ፍቃዱን መሰረዝ፤ወይም

(ሸ) ሌላ አግባብ ያለው እርምጃ፡፡

2. በጉዳዩ ላይ ባለሙያው የሚሰራበት የጤና ተቋም ለስነ-ምግባር ግድፈቱ አስተዋጽኦ ካለው ኮሚቴው ይህንኑ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ ማሳወቅ እና አግባብ ያለው እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (1) ስር ከ (ሀ) እስከ (መ) የተዘረዘሩት ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃ ተብለው ይመደባሉ፤
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (1) ስር ከ(ሠ) እስከ (ሰ) የተዘረዘሩት እርምጃዎች ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ ተብለው ይመደባሉ፤
5. ኮሚቴው ቅሬታ የቀረበበት የስነ-ምግባር ግድፈት ክብደት፣ ባህሪ፣ በጤና ላይ ያደረሰውን ጉዳት እና ሌሎች አግባብ ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት በቀላል ወይም በከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚያስቀጣ ይወስናል፤
6. በዚህ አንቀጽ መሰረት ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚያስወስድ የስነ-ምግባር ግድፈት ከፍተኛየጤናችግርሊያስከትልየሚችልሲሆንወይምበሰውላይሞትየሚያስከትልእናወይምበወንጀ ልተጠያቂነትየሚያስከትልድርጊትነው፤
7. በዚህ አንቀጽ መሰረት ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃ የሚያስወስድ የስነ-ምግባር ግድፈት የተፈፀመውተግባርሊያስከትልየሚችለውጉዳትአነስተኛከሆነወይምደግሞበህይወትወይምበጤናላ ይምንምአይነትጉዳትየማያስከትልሲሆንነው፤
8. ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃን የሚያስከትል የስነ-ምግባር ግድፈትን በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ የፈጸመ ባለሙያ በከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ ይቀጣል፡፡

## አንቀጽ 27
## ይግባኝ

1) በፍሬ ነገር ላይ የተላለፈው ውሣኔ የጸና ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ውሣኔው የተላለፈበትአካል ኮሚቴው ውሣኔውን ሲያስተላልፍ ህግ ወይም ስነ-ስርአት ጥሷል ብሎ ካመነበት ውሣኔው በተላለፈ በሰላሳ ቀን ውስጥ አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊል ይችላሉ፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (1) መሰረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት አቤቱታውን ከተቀበለው እና እንደገና እንዲታይ ትዕዛዝ ካሰተላለፍበፍርድ ቤቱ ግኝት መሰረት ጉዳዩ እንደገና በኮሚቴው እንዲታይ ይደረጋል፡፡

Directive on Health Professionals Ethics Committe

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 28

### የኮሚቴው አባላት ክፍያ አሰጣጥ

1. የኮሚቴው አባላት ክፍያ የሚወሰነው በቢሮው ለዚህ አላማበሚወጣው መመሪያ ይሆናል፤
2. በአገሪቱ ህግ የሚተዳደር ማንኛውም የኮሚቴው አባል አሰሪ የሆን ድርጅትየኮሚቴው አባል ስራውን በአግባቡ እንዲሰራ ፈቃድ ሊሰጠው ይገባል፡፡

### አንቀጽ 29

### የመተባበር ግዴታ

ቢሮው ይህን መመሪያለማስፈፀምእንዲችልጉዳዩየሚመለከታቸውማንኛውምየፌደራል እና የክልልመንግስት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

### አንቀጽ 30

### ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ ሰርኩላር ደብዳቤ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### አንቀጽ 31

### መመሪያ ስለማሻሻል

ቢሮዉ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜ መምሪያዉን ሊያሻሻል ይችላል፡፡

### አንቀጽ 32

### መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው ከህዳር12 ቀን 2008ዓ/ምጀምሮ ይሆናል፡፡

ሳላህ እስማኤል ኢብራሂም

የቤ/ጉ/ክ/መ/ ጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ

Directive on Health Professionals Ethics Committe